# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 147 መጋቢት 1 2003 ገጽ 1


የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች ለአስርት ዓመታት በአምባገነን አገዛዝ ተገዝተዋል። እኛ ደግሞ ለአስርት ዓመታት አምባገነን ብቻ ሳይሆን ዘረኛም ጭምር በሆነ አገዛዝ እየተገዛን ነው። እኛ እየደረሰብን ያለውን ዓይነት አዋራጅ ዘረኝነት እነሱ ላይ አልደረሰባቸውም። አምባነንነት እነሱን አስመርሮ በገዚዎቻቸው ላይ በአንድነት እንዲነሱ አድርጓቸዋል። እኛ ዘንድ ደግሞ አምባገነንነትና ዘረኝነት ተዳብለውብናልና ከእነሱ በላይ አምርረን በህብረት እንነሳለን።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በጋሞጎፋ ዞን የ8 ወረዳዎች ህዝብ ለወያኔ አልገዛም በማለት ተነሳ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት የውስጥ ምንጮቹን በመጥቀስ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓም ባወጣው ዘገባ በጋሞጎፋ ዞን የ8 ወረዳዎች ህዝብ ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ እያደረሰበት ባለው ግፍና በደል በመማረር ለወያኔ አልገዛም በማለት መነሳቱንና አካባቢውም በፌደራል ፖሊስና ጦር ሃይል መወረሩን ገልጹአል::

ኢሳት በዘገባው ላይ እንደገለጸው በስምንቶቹ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙት የመንግስት ሰራተኞች ተባረዋል፣ ትምህርት ቤቶችም ተዘግተዋል:: ህዝባዊ አመጹ ከተቀሰቀሰ ወዲህ ህዝቡ ወያኔ ከንግዲህ በጉልበት ካልሆነ በፍላጎት አይገዛንም የሚል የጸና አቋአም ይዙአል::

በጋሙጎፋ ዞን ስምንት ወረዳዎች ውስጥ የተነሳውን አመጽ ተከትሎ ከአስራ አንድ በላይ ንጹሃን ተገድለዋል በመቶዎች የሚቆጠሩ ታስረዋል:: ባልተጠበቀ አቅጣጫና ሁኔታ የተነሳው ህዝባዊ አመጽ ያደናበረው የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ፣ ከህዝቡ ጋር እንደራደር በማለት ሚኒስትሩን ቢልክም ህዝቡ ድርድር አንፈልግም ማለቱን ኢሳት በዘገባው ላይ ገልጹአል::

በቱኒዚያ የተነሳው ህዝባዊ አመጽ የሰሜን አፍሪቃ በርካታ ሃገራትን ካዳረሰ ወዲህ በኢትዮጵያ ህዝባዊ አመጽ መነሳቱ እንደማይቀር በርካቶች የገለጹ ሲሆን የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ የውሸት ቁንጮ በረከት ስምኦን የኢትዮጵያ ህዝብ በተደላደለ ኑሮ ላይ የሚገኝ በመሆኑና የነገዋን ኢትዮጵያም ብሩህ ተስፋ እየተመለከተ በመሆኑ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ አይችልም በማለት መናገሩ ይታወቃል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የእስልምና እምነት ተከታዮች በጂማ ክርስትያኖች ላይ እያደረሱ ባሉት ወንጀሎች የወያኔ እጅ እንዳለበት ታወቀ

ህዝብን በዘር በሃይማኖትና በጎሳ በመከፋፈል የስልጣን እድሜውን ማራዘም ስራየ ብሎ የተያያዘው ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ፡ በቱኒዚያ የተነሳው ህዝባዊ አብዮት በኢትዮጵያችን ሊነሳ ይችላል ከሚል ስጋት ለዘመናት ተፋቅሮ እና ተከባብሮ በሚኖረው የሙስሊሙና ክርስቲያኑ ህብረተሰብ መካከል ሆን ብሎ ግጭቶችን እየቀሰቀሰ መሆኑን ለሥር ዓቱ ቅርበት ያላቸው የግንቦት 7 ታማኝ ምንጮች ገለጹ።

ቀደም ሲል በአገዛዙ ሥር ባሉ ሚዲያዎችና ታላላቅ ስብሰባዎች ሳይቀር በወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ይነዛ የነበረው ጸረ አማራ ቀሳቀሳ እንደታሰበው አማራውንና የተቀረውን ህዝብ ሆድና ጀርባ ሊያደርግ እንዳልቻለ ወያኔ በምርጫ 97 ከደረሰበት ሽንፈት ልምድ ካገኘ ወዲህ ፡ የብሄረሰብን ልዩነትን ማራገቡን ለወጥ አድርጎ በሃይማኖቶች መካከል ውጥረት መፍጠር እንደቀጠል ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል። በአዲስ አበባ እና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች የመስጊድ ወይም የቤቴክርስቲያን መስሪያ ቦታ ሁለቱን ሃይማኖቶች ሊያራኩት በሚችል ሥፍራ እያስቀመጠ የተለያዩ ግጭቶችን ሲቀሰቅስ የቆየው ዘረኛው የመለስ ዜናዊ ቡድን የአንዱ ሃይማኖት አስተማሪ የሌላውን ዕምነት በአደባባይ እንዲያጥላላ ወይም እንዲያንቋሽሽ ሲያደርግ እንደነበረ የተለያዩ አገር ውስጥ የሚታተሙ ጋዜጦች አጋልጠዋል።

ህዝብ በወያኔ የ20 አመት አገዛዝ ክፉኛ በመማረሩ እና ለካድረዎችና ለወያኔ ጄሌዎች አልታዘዝም ማለት በመጀመሩ ሰሞኑን በሰሜን አፍርካ የታየው አይነት ህዝባዊ አብዮት ይነሳብኛል ከሚል ስጋት በህዝብ መካከል መተማመንና የአላማ አንድነት እንዳይኖር ለጂማ ከተማ ቅርብ በሆነቹው አሰንዳቦ ከተማ ሙስሊሞች ተነስተው ቤቴክርስቲያን በእሳት እንዲያጋዩና ክርስቲያኖችን አካባቢውን ለቀው እንዲጠፉ የወያኔ አጋር በሆኑት የክልሉ ባለሥልጣናት አማካይነት እየተሰራ መሆኑን መረጃ ምንጮቻችን አጋልጠዋል።

ይህ በጂማ እና አካባቢው እየተባባሰ ያለውን የሃይማኖት ግጭት ለማስቆም ወያኔ አስከ ዛሬ የወሰደው ምንም እርምጃ እንደሌለ የሚናገሩ ምንጮቻችን በአስንዳቦ ወረዳ ብቻ ከ7 ሺህ በላይ ክርስቲያኖች መፈናቀላቸውን ገልጸዋል። የግንቦት7 ዘጋቢ በግጭቱ የተፈናቀሉትን የጥቃቱን ሰለባዎች አሻኝቶ ያነጋገረ ሲሆን ግጭቱ በህይማኖት ምክንያት የተነሳ ይሁን እንጂ ወያኔ ህዝብን በመከፋፈል ለመግዛት ያለውን አጀንዳ ለመተግበር ሆን ብሎ እርስ በርስ እንደሚያጋጫቸው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እንደሚያውቁ እንደነገሩት አስታውቆአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

## የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ ባለቤት የሆነቺው አዜብ መስፍን የቅንጦት ኑሮ መጋለጡን ቀጥሉአል

የዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ለሸቀጣ ሸቀጥ ሸመታ የካቲት 19 ቀን 2003 አም በቻርተር አውሮፕላን ወደ ዱባይ በረራ አድርጋ እንደነበር የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን የአየር መንገድ ምንጮችን በመግለጽ ዘግቦአል። እንደ ኢሳት ምንጮች መረጃ አዜብ መስፍን በደህንነት ሰዎች ታጅባ በቤተመንግሥት መኪና ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ከደረሰች ቡኋላ ያለምንም ፍተሻና ቁጥጥር በልዩ መግቢያ በር ወደ ውስጥ እንድትገባ ተደርጎ 12 ሰዎችን ብቻ ለመጫን በተዘጋጀ ቻርተር አውሮፕላን ከሁለት አጃቢዎቿና ከአንዲት የውጪ አገር ዜጋ ከሆነች ሴት ጋር ወደ ዱባይ ተጉዛለች። ዱባይም እንደደረሰች በዱባይ የወያኔ ኤምባሲ ሰራተኞች የክብር አቀባበል ከተደረገላትና ወደ ኤምባሲው ማረፊያ ከተወሰደች ቡኋላ ወድ በሆነ የሚኾት መኪና የቅንጦት ዕቃ ወደሚሸመትበት የተዋቡ ሱቆች እንደተወሰደች የኢሳት የአየር መንገድ ምንጮች አጋልጠዋል።

በሚያማምሩ የዱባይ ህንጻዎች ውስጥ ለሃብታሞች ብቻ በተዘጋጁት ውድ ሱቆች የምትፈልገውን ሁሉ ዕቃ በውጭ ምንዛሪ የሸመተቺው አዘብ መስፍን፤ የገዛቺውን እቃዎች በሙሉ የኤምባሲው ሰራተኞች ለኢትዮጵያ ዓየር መንገድ እንዲያስረክቡ ትዕዛዝ በመስጠት ከነ አጃቢዎችዋ በመጣችበት ቻርተር አውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ተመልሳለች:: አዜብ መስፍን የሸመተቻቸው እቃዎች በጠቅላላ ወደ ለንደን በሚበር የኢትዮጵያ ዓየር መንገድ ተጭኖ እንደሄደና ከባለበቷ መለስ ዜናዊ ጋር በለንደን ከተማ በገዙት የግል መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደሚቀመጥ መረጃው ያመለክታል። ለንደን ከተማ የሚገኘውን አዲሱን መኖሪያ ቤታቸውን በሃላፊነት የሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝብ በሚከፍለው ግብር ደመዎዝ የሚከፈለው በዩናይትድ ክንግደም የኢትዮጵያ አምባሳደር ተብሎ የተሰየመው ብርሀኑ እንደሆኑ ታውቁአል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ አርሶ አደሮችን የፓርቲ አባል ካልሆናችሁ እያለ በማንገላታት ላይ መሆኑ ተገለጸ

ህዝብን እንደ ጠላት እየፈራ ያለው የወያኔ ዘረኛ ቡድን ሰሞኑን በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ አርሶ አደሮችን የልማት ስብሰባ በማለት እየጠራና የፓርቲው አባላት እንዲሆኑ እያስገደዳቸው መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ከላከልን መረጃ ለማወቅ ተችሎአል። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በቱኒዚያ ፈንድቶ የሰሜን አፍሪቃ ሃገራትን እየለበለበ ያለው የህዝብ አመጽ እንደማይቀርለት የተረዳው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ የህዝብ ተቃውሞ ወደገጠሪቱ የሀገሪቱ ክፍል እንዳይስፋፋ በማሰብ በአርሶ አደሩ ዘንድ መፈራራትንና አለመተማመንን ለመፍጠር በማሰብ ከየዞኑ የሰበሰባቸውን አርሶ አደሮች አባል ካልሆናችሁ እርዳታ አናደርግላችሁም፤ የያዛችሁትንም የእርሻ መሬት ተቀብለን ለሌሎች እናከፋፍላልን እያለና እያስፈራሩ አባል እንዲሆኑ ያስገደዳቸው ሲሆን አርሶ አደሮቹ ወደመኖሪያቸው ቦታ ሲመለሱ እያንዳንዳቸው በስራቸው አምስት አምስት ሰዎችን እንዲያደራጁና የድርጅቱ አባል እንዲሆኑ እንዲያደርጉ መመሪያ እንደተሰጣቸው ታውቁአል።

ይህም ተግባር በተለያዩ የሀገሪቱዋ ክፍል ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን በተለይ በሰሜን ሸዋ ወራ ጃርሶ ወረዳ፣ በኢሊባቡር- በደሌ አካባቢ፣ በአርሲ- አሳሳ፣ ዶዶላ እና ኮኮሳ ወረዳዎች ላይ ሁኔታው መባባሱና በነዚህም አካባቢዎች የሌላ ፓርቲ አባላትን ያለምንም ምክንያት እስር ቤት በመወርወር መንቀሳቀሻ እንዳጡ ለማወቅ ተችሎአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ በያዝነው የበጀት አመት ወደ ውጪ የላከው የቡና ምርት በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰ መሁኑ ተዘገበ

በያዝነው የበጀት አመት አጋማሽ ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ ሃገር ይልካል ተብሎ የታቀደ የቡና ምርት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን ሮይተርስ የተባለው የዜና አውታር ዘገበ። እንደዘገባው ከሆነ በአፍሪካ በቡና አቅራቢነቱዋ የምትታወቀው ሃገራችን ከምርቱ ከፍተኛ ገቢ በማግኘት በዘርፉ ላይ የተሰማሩትን ገበሬዎች ማጠናከር ብሎም ከድህነት አረንቁዋ ማውጣት የምትችልባቸው አጋጣሚዎች ሰፊ ሆነው ሳሉ ወያኔ በተገቢው ማከናወን አለመቻሉ በርካታ ታዛቢዎችን እንዳስገረመም አክሎ ገልጾአል።

መለስና ግብረአበሮቹ በተለያየ ስም ባቋቋሙዋቸው ድርጅቶቻቸው በገሀድ ከሚያደርጉዋቸው የውጭ ንግድ በተጨማሪ በድብቅ ወደውጭ ሀገራት በመላክ የሚሸጡዋቸው ምርቶች ሀገሪቱዋ ከፍተኛ ገቢ እንድታጣ ማድረጋቸውን ገልጹአል:;

ኢትዮጵያ የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት ወደ ውጭ ከምትልካቸው ምርቶች አንዱ ቡና ሲሆን መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ በፍጠንት ለመክበር ካላቸው ራስ ወዳድነት የተነሳ ሁሉንም የንግድ ዘርፎች በመቆጣጠር ከፍተኛ ትርፍ በማጋበስ ላይ የሚገኙ ብቻ ሳይሆን በዘረፉ የሚገኘውን ገንዘብ ከኢትዮጵያ ህዝብ በማሸሽ በውጪ አገር ባንኮች በማካበት ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል። ወደ ጎረቤት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# አዎ! ይቻላል!!!

የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ “ቱኒዚያዊያን፣ ግብጾች፣ የመኖች፣ ሊቢያዊያን እና ሌሎች የአካባቢው አገር ዜጎች ማድረግ የቻሉትን እናንተ ማድረግ አትችሉም፤ ፈጽሞ አታስቡት” እያለን ነው። ውሸት ማውራት ሥራቸው የሆነው የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን “በመለስ ዜናዊ ሥልጣን ላይ አንዳች ተቃውሞ ከተቃጣ አገሪቱ ትታመሳለች” በማለት ያስፈራራሉ። የመለስና ቤተዘመዶቹ ደካማና ዘረኛ ድርጅትን ግዙፍና የማይደፈር አድርገው ያቀርባሉ። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ለልጆታቸው ባርነትና ፈሪነትን እንዲያስተምሩ ያበረታታሉ፤ “ልጆቻችሁን ጠብቁ” እያሉም ይሰብካሉ፤ ያሰብካሉ።

እኛ ግን “የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች ማድረግ የቻሉትን እኛ ኢትዮጵያዊያን ማድረግ የማንችልበት ምክንያት የለም” እንላለን። እራሳችንን ከሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች ጋር ባወዳደርን መጠን ደግሞ ልበ ሙሉነት ይሰማናል።

1. የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች ለአስርት ዓመታት በአምባገነን አገዛዝ ተገዝተዋል። እኛ ደግሞ ለአስርት ዓመታት አምባገነን ብቻ ሳይሆን ዘረኛም ጭምር በሆነ አገዛዝ እየተገዛን ነው። እኛ እየደረሰብን ያለውን ዓይነት አዋራጅ ዘረኝነት እነሱ ላይ አልደረሰባቸውም። አምባነንነት እነሱን አስመርሮ በገዢዎቻቸው ላይ በአንድነት እንዲነሱ አድርጓቸዋል። እኛ ዘንድ ደግሞ አምባገነንነትና ዘረኝነት ተዳብለውብናልና ከእነሱ በላይ አምርረን በህብረት እንነሳለን።
2. እነሱ አገር ውስጥ ኑሮ በመወደዱና ሥራ በመጥፋቱ ድህነት አስመርሯቸዋል። እኛ አገር ደግሞ የዛሬ ኑሮዓችን ብቻ ሳይሆን የነገ ተስፋችን ጭምር ጠፍቶብናል። ለም መሬታችን ለባዕዳን ተሸጦብናል። እነሱ ያጡት ሥራ ነው፤ እኛ ግን አገርም የለንም። እኛ ከነሱ በላይ አምርረን ለመነሳት በቂ ምክንያቶች አሉን።
3. የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ሹሞች በሙስና ያካበቱት ሃብት በቢሊዮን ዶላሮች ይገመታል። የእኛ የመጨረሻይቱ ድሃ አገር ሹሞችም በሙስና ያካበቱት ሃብት በቢሊዮን ዶላሮች ይገመታል። እርግጥ ነው በከተሞቻችን ህንፃዎች በርክተዋል ሆኖም ግን የሙሰኞቹ እንጂ የለፍቶ አዳሪዎቹ አይደሉም። በሃብት መበላለጥ የተቆጩት እና በሙስና መብዛት የተናደዱ የአህጉራችን ዜጎች በገዢዎቻቸው ላይ ተነስተዋል። እኛ ደግሞ ከእነሱ በላይ ተጎድተናልና ከእነሱ በላይ አምርረን እንነሳለን።
4. የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች በያገራቸው ፍትህ በመጓደሉ ተማረዋል። እኛ አገር ደግሞ ፍትህ ራስዋ ተዋርዳለች። ፍርድ ቤቶች ማጥቂያዎች ሆነዋል። አገራችን እስር ቤት ሆናለች። አብዮት ከቀሰቀሱት ጎረቤቶቻችን በባሰ እኛ ተበድለናልና ከእነሱ በባሰ አምርረን እንነሳለን።
5. የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች ለዘመናት መብቶቻቸው ተገፎ “የታዘዛችሁትን አድርጉ፤ አንዳችም ነገር አትጠይቁ” ሲባሉ ኖረዋል። እኛም ለሃያ ዓመታት “እኛ ስንናገር እናንተ አጨብጭቡ፤ ከዚያ ባፈለ ግን አትጠይቁ” እየተባልን ነው። እነሱ “በቃን” ብለዋል፤ እኛም “በቃ - ጋዮ” ብለናል።

“ኢትዮጵያ ቱኒዝያ ወይም ግብጽ አይደለችም” የሚለውን ፕሮፖጋንዳ ሰልችቶናል። በቱኒዝያና ግብጽ ብቻ ሳይሆን በየመንና ሊቢያ ህዝብም ጥንካሬ እንኮራለን። ለአርባ ሁለት ዓመታት የተደራጀን ኃይል በሳምንታት ውስጥ በተፈጠረ የአማጽያን ኃይል እያርበደበደ ያለው የሊቢያ ህዝብ ጥንካሬ የልብ ልብ ሰጥቶናል።

በአምባገነን አገዛዝ መረገጥ በቃን!!!! የሰሜን አፍሪቃ እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ዜጎች ማድረግ የቻሉትን እኛ ኢትዮጵያዊያን ማድረግ እንችላለን። አዎ! እኛም እንችላለን! ይቻላል!!

በቃ- ጋዮ!!!!

## የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ፓርላማ ምክር ቤት ተሰናባቾች የካድሬነት ስራቸውን ጀመሩ

ከተለያዩ ክልሎች በህዝብ ተመርጠናል ብለው በፓርላማ ምክር ቤት የቆዩት የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ሆድ አደሮች ከፓርላማ ምክር ቤት ከተሰናበቱ በሁአላ እዚያው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች እንዲቀጠሩ ተደርገው የካድሬነትን ስራ እንዲያከናውኑ መመደባቸውን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በአስተላለፈልን ዘገባ ለመረዳት ችለናል:: እንደ ዘጋቢያችን ሪፓርት የቀድሞው የፓርላማ ምክር ቤት አባላት በአዲሶቹ ሆድ አደሮች ከተተኩ በሁአላ እንደ ማንኛውም የዘረኛው አገዛዝ ሆድ አደሮች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የመሬት ቅርምትና ቤትም የመስራት ዘመቻቸውን አጡዋጡፈውታል::

በኢትዮጵያ ህዝብ ተከሻ ላይ ተፈናጦ የሚገኘው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያንን በዘር በሃይማኖትና በጎሳ ከመከፋፈል በተጨማሪ ለሆዳቸው ያደሩ ዜጎችን በጥቅም በመደለል በቀሪው ህዝብ ላይ የሚፈልገውን ተግባር ማስፈጸሚያ እያደረጋቸው እንደቆየ ይታወቃል::

የነኝህን የቀድሞ የፓርላማ ምክር ቤት አባላት ወደየ ክልሎቻቸው አለመመለስና በአዲስ አበባ ከተማ የካድሬነት ተግባር እየፈጸሙ ያሉ መሆናቸውን አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት እነኝህ ካድሬዎች ድሮውንም ቢሆን ወያኔ የመለመላቸው እንጂ ህዝብ የመረጣቸው አልነበሩም:: ፓርላማ በቆዩበት ጊዜም ቢሆን ሲያከናንውኑ የቆዩት ተግባአር እጂ ማውጣትና ማውረድ እንጂ ምንም ለሃገርም ሆነ ለህዝብ የሚጠቅም አልነበረም:: እንዲያውም በአጠቃላይ አገር የማጥፋት ተግባርን ነው ሲያከናውኑ የቆዩት::

አሁንም እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ተቀምጠው የካድሬነት ተግባር መፈጸማቸው አያስገርምም፣ ምክንያቱም ህሊናቸውን ሸጠው ለሆዳቸእው ያደሩ ናቸውና ብለዋል:: በመጨረሻም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ዘረኛው አምባገነን አገዛዝ እንደፈለገ እንድዲጨማለቅ ላደረጉት አስተዋጸ ዋጋቸውን የሚያገኙበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ቀናቸውን ነው የሚቆጥሩት በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል::

## በአዲስ አበባ የኤሌክትሪክ ሃይልአ ቅርቦት እጥረትና የመጠጥ ውሃ ችግር እየተባባሰ ነው

በአዲስ አበባ ከተማ ቀደም ብሎ የነበረው የውሃና የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ችግር እንደተባባሰና በአንዳንድ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች በውሃ እጥረት ምክንያት ህብረተሰቡ አሁንም እየተጉላላ መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ:: እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በተከሰተው የውሃ እጥረት ምክንያት ነዋሪዎች ውሃ ፍለጋ ረጂም መንገድ ለመጉአዝ እየተገደዱ እንደሆነ አክሎ ገልፁአል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም በከተማይቱ አሁንም የኤሌክትሪክ አቅርቦት እጥረቱ እንደቀጠለና ይህም ችግር በርካታ ክፍለ ከተሞች ላይ እየተከሰተ መሆኑን ገልጹአል::

በአዲስ አበባ ከተማ ያለው የሙብራት ሃይል አቅርቦት ችግር በዚህ መልኩ ባለበት ሁኔታ ለዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ቅርበት እንዳለው የሚታወቀው ሪፖርተር ባወጣው ዘገባ ከበለስ የኃይል ማመንጫ ወደ አዲስ አበባ የተዘረጋውና ከ1.9 ቢሊዮን ብር በላይ የወጣበት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመርና የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ግንባታቸው ተጠናቁአል፡፡ የኤሌክትሪክ ሃይል ችግር ከንግዲህ አይኖርም ብሉአል::

የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ እየታየ ያለውን ችግር አስመልክቶ ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሰጡት አስተያየት መቼም ወያኔ ይቺን ሃገር እስከገዛ ድረስ ህዝቡ ከችግር ነጻ ይሆናል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው:: የጊቤ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግንብታ ተጀምሮና እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ወያኔ እየተከሰተ ላለው የሙብራት ሃይል እጥረት የማይቀባጥረው ነገርና የማይሰጠው ምክንያት አልነበረም። እነሆ ጊቤም ሆነ ተኬዜ ተመርቆ አገልግሎት እየሰጠ ነው ብንባልም እንደሚታየው ችግራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰበት እንጂ እየተሻለው ሲሄድ አይታይም ብለዋል፣ በመጨረሻም ችግራችንና የችግሮቻችን ምንጭ ወያኔና ወያኔ በመሆኑ ዛሬ ነገ ሳንል ባንድነት ተነስተን ከትከሻችን ላይ አሽቀንጥረንን መጣል ይኖርብናል በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል::

## በጋሞጎፋ ዞን የ8 ወረዳዎች ህዝብ ለወያኔ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ)

በሌላ በኩል የግንቦት ሰባት ዘጋቢ የታመኑ ምንጮቹን በመጥቀስ በላከልን ዘገባ በአዋሳ በተነሳ ግጭት በርካቶች እየታሰሩ መሆናቸውንና በአካባቢው የሚገኘው አርሶ አደርም በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በመማረሩ ፖሊሶችን ማባረሩና በፖሊሶች ላይም ጉዳት ማድረሱ ታውቁአል:: በአዋሳ የተከሰተው ውጥረቱ እንዳለ ሲሆን በተፈጠረው ሁከት መኪኖች ተሰባብረዋል:: በአዋሳ የተነሳውን ግጭት ለማብረድ በሚል የአዋሳ ከተማ ሆድ አደር ከንቲባ የአገር ሽማግሎዎችን ሰብስቦ ከመጤዎች ጋር አትቁሙ እያለ መምከሩን የደረሰን ዜና የገለጸ ሲሆን ህዝቡ ግን ለዘመናት ተፋቅረን ከኖርነው ከመጤው ህዝብ ጋር አታጣሉን እያለ መሆኑ ታውቁአል::

በበረከት ስምዖን ሃላፊነት ሥር የሚተዳደረው የወያኔ መገናና ብዙሃን በቲኒዚያ እና ግብፅ የተካሄደውን ህዝባዊ አብዮት የአየር ሽፋን ሳይሰጡት ከሰነበቱ ቦኋላ የሊቢያ ህዝብ የቀሰቀሰውን ህዝባዊ አብዮት ለመቀልበስ ሙአመድ ጋዳፊ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ እየወሰዱ ያሉትን ጨካኝ እርምጃ እየተከታተሉ በማቅረብ ላይ እንዳሉ ይታወቃል። በአገሪቱ ግብር ከፋይ ገንዘብ የዘረኛውን ወያኔ እድሜ ለማራዘም ህዝባችንን በባዶ ተስፋና ፕሮፖጋንዳ ለማደንዘዝ የተሰለፈው የኢትዪጵያ ቴሌቭዥን ጣቢያም በሰሜን አፍርካ የተነሳው ህዝባዊ አመጽ በአገራቺን ሊከሰት የሚችልበት ምንም መሠረት የለም ከማለት ጀምሮ በአጋጣሚ ቢከሰት እንኳ ወያኔ ያስገኘውን ልማት እና እድገት ያወድማል እንጂ ህዝብ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችል ፋይዳ ያለው ለውጥ አያስገኝም የሚል ቅስቀሳ በማሰራጨት ሥራ መጠመዱ ታውቆአል።

## የመጨረሻዉ ደወል

ከሁለት ምዕተ አመታት በፊት ትልቅነቷ ተዳስሶ የማያልቅ ትመስል የነበረቺዉ ይቺ የምንኖርባት ምድር ዛሬ ቴክኖሎጂ እንደ አበሻ ቀሚስ ጥለት ጠልፎና አጠላልፎ ሁሉም ሰዉ በአንድ ግዜ መተያየት የሚችልበት ክብ ጠረቤዛ አስመስሏታል። ዛሬ የአሜሪካ ህዝብ ምሽት ላይ የሰማዉን ሰበር ዜና አፍሪካን ጨምሮ የሌላዉ ዓለም ህዝብ የሚሰማዉ አሜሪካኖች ዜናዉን የሰሙበትን የቴሌቭዥን ጣብያ ሳይቀይሩት ነዉ። ይህ የሚያሳየን ወደ አገሮች ዉስጥ የሚገባዉና ከአገሮች የሚወጣዉ ዜና ሙሉ በሙሉ በአምባገነን መሪዎች ቁጥጥር ስር የነበረበት ዘመን ዳግም ላያንሰራራ ማክተሙን ነዉ። አገራችን ኢትዮጵያን እንኳን ብንመለከት የአምባገነኑ መንግስቱ ኃ/ማሪያምን ግፍና ሰብዓዊ መብት ረገጣ የዉጭዉ አለም የሚሰማዉ ዜናዉ በወሬ ነጋሪ ከአገር ወጥቶ ዉሎ አድሮ ከሰነበተና የወሬ ቋንጣ ከሆነ በኋላ ነበር። ዛሬ ግን የዘመኑ ቴክኖሎጂ ምስጋና ይግባዉና የወያኔ ዘረኞች የሚፈጽሟቸዉን አፈናዎችና ግድያዎች የአለም ህዝብ የሚሰማቸዉና አንዳንዶቹን በምስል በተደገፈ መረጃ የሚመለከታቸዉ ከመቅጽበት ነዉ። ይህንን ቅጽበታዊ የሆነ የመረጃ ልዉዉጥ ይበልልህ የምንለዉ አለማችንን በማቀራረቡ ብቻ ሳይሆን እንደ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ አይነቶቹን አምባገነን መሪዎች እርቃናቸዉን እንዲቀሩ ማድረግ በመቻሉ ነዉ። ይህ በመሆኑ ይመስላል ዛሬ የወያኔ አገዛዝ ከ3 ሚሊዮን በላይ ዜጎቼ ለረሀብ አደጋ ተጋልጠዋል ብሎ ለምፅዋት በዘረጋበት እጁ ያንኑ የተራበ ህዝብ ከመረጃ ዉጭ ለማድረግና ጨለማ ዉስጥ ለማቆየት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር በልመና የተገኘ የህዝብ ገንዝብ የሚያባክነዉ።

በቅርቡ ቱኒዝያና ግብፅ ዉስጥ የተካሄዱትና እጅግ በጣም አጭር በሆነ ግዜ ዉስጥ ሁለት የለየላቸዉ አምባገነን መሪዎችን አሽቀንጥረዉ የጣሉት ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች የመረጃ ቴክኖሎጂ ዉጤቶች ናቸዉ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ግብፅና ቱኒዝያ ዉስጥ በአይን ተያይቶ የማያዉቅ ህብረተሰብ በተለይም ወጣቱ ትዉልድ በማይታይና በማይዳሰስ አለም ዉስጥ ተገኛኝቶና መክሮ የጀመረዉን ንቅናቄ ከግቡ እንዲያደርስ የረዱት እንደ ፌስ ቡክ፤የእጅ ላይ ስልክ፤ቲዉተርና እንተርኔትን የመሳሰሉ የመረጃ ቴክኖሎጂ ዉጤቶች ናቸዉ። ቴክኖሎጂ ግዑዝ አካል ነዉና በራሱ የሚሰራዉ ወይም የሚለዉጠዉ ምንም ነገር የለም። ቴክኖሎጂ አንድን ህብረተሰብ በሚገባ እንዲያገለግል በአንድ በኩል የሚያስፋፋዉ በሌላ በኩል ደግሞ አዘዉትሮ የሚጠቀምበት የህብረተሰብ ክፍል ያስፈልጋል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ አገሮች ዉስጥ ወጣቱ ትዉልድ ከቴክኖሎጂ ጋር ለመተዋወቅ ያለዉ ፍላጎትና ዝንባሌ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ። ሆኖም ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ የወጣቱን ከቴክኖሎጂ ጋር መተሳሰር የሚያገናኘዉ ከአገር ልማትና እድገት ጋር ሳይሆን ከራሱ የስልጣን ዘመን ማክተም ጋር ስለሆነ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተስፋፋዉ ህዝብን የሚያስተሳስርና አገርን የሚያለማ ቴክኖሎጂ ሳይሆን ድህረ ገጾችን፤ሬዲዮ ጣቢያዎችንና የቴሌቭዥን ጣቢያዎችን የሚያፍን አስቀያሚና ጎታች ቴክኖሎጂ ነዉ። ስለሆነም ዛሬ ኢትዮጵያ በኢንተርኔት አጠቃቀም በአለም ላይ የመጨረሻዋ አገር ናት።

የግብፅ ህዝብ በልዕለ ኃያሏ አገር አሜሪካ በከፍተኛ ደረጃ የሚታገዘዉ የሆስኒ ሙባረክ አገዛዝ የማይነካ እየመሰለዉ የሙብትና የነፃነት ጥያቄዉን በፍርሀት ሸብቦት ለብዙ ዘመን በጨለማ ዉስጥ ኖሯል፤ ሆኖም ፍርሀት መቼም ሆነ ዬትም ቦታ ገደብ አለዉና የግብፅ ወጣቶች ፍርሀታቸዉን ተጋፍጠዉ በከፍተኛ የደህንነት ሀይል፤ በመረጃና በስለላ ስራ የተካነዉን የሞባረክ አገዘዝ በ18 ቀን ዉስጥ ብትንትኑን ማዉጣት ችሏል። ከዚህ አጅግ አስገራሚ ከሆነ ህዝባዊ ድል የአለም ጭቁን ህዝቦች በተለይም በዘረኞችና በጎጠኞች በትር ቀንና ማታ የሚደበደበዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ የሚማራቸዉ ነገሮች አሉ። በእርግጥ በግብፅና በኢትዮጵያ ህዝብ መካለከል የባህል፤የታሪክ፤የቋንቋና የኤኮኖሚ እድገት ልዩነቶች አሉ፤ ሆኖም ግብፃዉያንን "ዛሬስ በቃ" አሰኝቶ ካነሳሳቸዉ የኤኮኖሚ፤ የፖለቲካና የማህበራዊ ችግር የበለጠና እጅግ የተወሳሰበ ችግር ኢትዮጵያ ዉስጥ አለ። አንድ የግብፅ ዜጋ በአመት የሚያገኘዉ የነፍስ ወከፍ ገቢ አስር ኢትዮጵያዉያን ከሚያገኙት ተመሳሳይ አመታዊ ገቢ ይበልጣል፤ እንግዲህ እኛ ኢትዮጵያዉያን አስር ሆነን ከምናገኘዉ ገቢ በላይ የሚያገኘዉ ግብፃዊ ድህነት መረረኝ ብሎ ከተነሳ እኛማ ድህነትና ዘረኝነት እንደ ገና ዳቦ ከላይና ከታች የሚለበልበን ኢትዮጵያዉያን አምርረን ብንነሳ ከዉርደትና ከእርግጫ ሌላ ምን የሚቀርብን ነገር ይኖራል? አዎ- ብዙዎቻችን የወያኔ እስከዛሬ በሥልጣን ላይ መቆየት ጸጽቶናል፤ ሆኖም ባለፈዉ እየተፀፀተና የወደፊቱን ከወዲሁ እየፈራ የሚኖር ህብረተሰብ ግፈኞች እንደ ጭነት ከጫኑበት ቀንበር መላቀቅ አይችልምና የኢትዮጵያም ህዝብ እንደ ግብፅ እንደ ቱኒዝያና እንደ ሊቢያ ህዝብ "ሆ" ብሎ የሚነሳበትን ቀን ካሁኑ መምከርና ማመቻቸት ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ ከምን ግዜም በላይ እጅግ በጣም ወሳኝና ወስብስብ ወደሆነ የፖለቲካ ምዕራፍ ዉስጥ እየገባ ነዉ፤ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ከዚህ እጅግ አሳሳቢ ከሆነ ታሪካዊ ዝቅጠት መንጥቆ ለማዉጣት በሚደረገዉ የሞት የሽረት ትግል ዉስጥ ከፍተኛዉን ሚና መጫወት ያለባቸዉ ሁለት የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ - እነሱም የለዉጥ አንቀሳቃሽ የሆነዉ የወጣቱ ትዉልድና ኢትዮጵያን ከዉጭም ሆነ ከዉስጥ ጠላቶች የመከላከል ታሪካዊ አደራ የተቀበለዉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ነዉ ። የወያኔ የስልጣን ዘመን በረዘመ ቁጥር የወደፊቱ የሚጨልምበትና ስቃይና ዉርደቱ የሚበዛበት የወጣቱ ትዉልድ ሲሆን፤ በአንፃሩ የወያኔ ስርዐት ፈርሶ ኢትዮጵያ ዉስጥ የእኩልነት ስርዐት ሲመሠረት ከማንኛዉም የህብረተሰብ ክፍል በላይ ተጠቃሚ የሚሆነዉ ይሄዉ የወጣቱ ህብረተሰብ ነዉ። አብዛኛዉ አባላቱ በወጣትነት ዕድሜ ክልል ወስጥ የሚገኘዉ የኢትዮጵያ የመከላኸያ ሠራዊት ደግሞ የወያኔ ዘረኝነትና ጋጠወጥነት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ካዋረዳቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱና ዋነኛዉ ነዉ። ስለሆነም ሠራዊቱ ለዉጥ እንደ ዉኃ የጠማዉ ሠራዊት ነዉና ዘረኞች ለዉጥን እንዲዋጋና ወንድሞቹንና እህቶቹን እንዲገድል በየጎዳናዉ ቢያሰማሩትም ይህ ሠራዊት የህዝብ ልጅ ነዉና እንደ ቱኒዝያና እንደ ግብፅ ሠራዊት ህዝባዊዉን እንቅስቃሴ ይቀላቀላል እንጂ እናትና አባቱ ላይ አይተኩስም የሚል የፀና እምነት አለ።

የወያኔ መሪዎች ያሻቸዉን ያክል ሊገድቡት ቢሞክሩም የሰሜን አፍሪካን አምባገነኖች የጠራረገዉ ህዝባዊ ማዕበል እነሱንም ጠራርጎ የታሪክ ቆሻሻ ዉስጥ መጨመሩ የማይቀር ነዉ። ሆኖም ዛሬ የአምባገነኖች ባህል ነዉና "እሳት ሳይቀጣጠል በቅጠል" እንዲሉ ቱኒዝያና ግብፅ ዉስጥ የተቀጣጠለዉ የነፃነት ሰደድ እሳት የኢትዮጵያን ድንበር እንዳያልፍ ለመገደብ ቁጭ ብድጉን ተያይዘዉታል። ከሰሞኑማ የጂቡቲዉ ጉዳይ አስደንግጧቸዉ ግዑዙን ባቡር ጭምር ይጠራጠሩት ጀምረዋል። የሰሞኑ የአዲስ አበባና የሌሎችም ትላልቅ ከተማዎች ሁኔታ በግልፅ እንደሚያሳየን ሰርግና ምላሹ እንዳከተመ የገባቸዉ የህወሀት መሪዎች በከፍተኛ ፍርሀት ተዉጠዋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለአገር አንድነት የሚቆረቆርና ለህገመንግስት የሚገዛ የመከላከያ ተቋም ኢትዮጵያ ዉስጥ እንደሌለ በዉል የሚያዉቀዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አምናና ካቻምና ከደረሰበት ሰቀቀን ዛሬም አልተላቀቀም። ስለሆነም ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ በግልጽ የሚታያዉ ወያኔ ህዝብን ከዛሬ ነገ ተነሱብኝ እያለ ሲፈራና የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ዘንድሮ "ምን ያመጡብን" ይሆን እያለ ወያኔዎችን ሲፈራ ነዉ።

ከፍርሀት ዉጭ የሆነ ግለሰብም ሆነ ህብረተሰብ የለም- አልነበረም- አይኖርምም! ግብፃዉያንና ቱኒዝያዉያን ለረጂም ግዜ በፍርሀት ጥላ ስር ኖረዋል። የእነዚህ ሁለት አገሮች ህዝብ ዛሬ የአለማችን የለዉጥ ማዕበል ተምሳሌት የሆነዉ አብሮት የኖረዉ ፍርሀት በቀድዶ ጥገና ከዉስጡ ወጥቶለት ሳይሆን ፍርሀቱን ፊት ለፊት ተጋፍጦ ነዉ። እኛ ሰዎች ክንዳችን የሚበረታዉ ተስፋችን የሚለመልመዉና በራስ መተማመናችን የሚጠነክረዉ እዉስጣችን ያለዉን ፍርሀት ጥሰን ወደ ፊት መጓዝ ስንችል ብቻ ነዉ። የነገዉ የነፃነት ራዕያችን ስፋትና ርዝመት ዛሬ ከርችሞ የያዘንን የፍርሀት ጥልቀት ዘልሎ ማለፍ ካልቻለ የሚጠብቀን ነገር ቢኖር ባርነት ብቻ ነዉ። ባርነት ደግሞ የማንም አማራጭ አይደለም!

ባለፉት ሀያ አመታት ወያኔ የ17 አመት የበረሃ ልምዱንና ወደር የለሽ ጭካኔዉን እያሳየን ሆን ብሎ የፍርሀት መንፈስ ሲረጭብን ቆይቷል። ይህ የተቀነባበረ የወያኔ አፍዝ አደንግዝ የፍርሀት ዘመቻ ደግሞ የዋሁን የህብረተሰባችን ክፍል ብቻ ሳይሆን ለጭንቅ ቀን ይሆኑናል ብለን ያስተማርናቸዉን አንዳንድ ምሁራን ጭምር አዘናግቶ የወያኔን ጥንካሬና ትልቅነት እንዲነግሩን አድርጓቸዋል። የሚገርመዉ እነዚህ ስማቸዉ ላይ ፕሮፌሰርና ዶክተር የሚል ቅጥያ የተቀጠለላቸዉ ምሁራን እነሱ ተምቦቅብቀዉ እኛም እንደነሱ እንድንፈራ የሚነግሩን ይህንን መለስ ዜናዊና ስብሐት ነጋ ጠፍጥፈዉ የሰሩትን ወያኔ የሚባል የዘረኞች ስብስብ ሳይሆን የራሳቸዉ ፍርሀት አምጦ የወለደዉን ወያኔ ነዉ - አለዚያማ ወያኔ ህዝብን ከዛሬ ነገ ይነሳብኛል እያለ በሚፈራበት ዘመን ህዝብ ወያኔን የሚፈራበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይገባም። እኛ ኢትዮጵያዉያን ባለፉት ሃያ አመታት ለሠላም፤ለፍትህ፤ ለነፃነትና ለእኩልነት እጅግ በጣም መራራ ትግል አካሂደናል፡ ነገር ግን ስለ ድልና ስለ ጀግንነት ከሚነግረን የውስጥ ስሜታች ይልቅ ወያኔ በጆሯችን ሹክ የሚለንን የፍርሃት ሹክሹክታ በማዳመጣችን ወዳለምነዉ ግብ መድረስ አልቻልንም።

ነፃነቱንና ሰብዓዊ ክብሩን የተቀማ ህዝብ ገዢዎቹን ፈርቶና ሰጥለጥ ብሎ አንገቱን ደፍቶ የኖረበትን አጋጣሚ ታሪክ መዝግቦት አያዉቅም። የሰዉን ልጅ ከሌላዉ ፍጡር የሚለየዉ ዋናዉ ነገር ነፃነቱን ተቀምቶ ትርጉም የለሽ ኑሮ ከሚኖር ለነፃነቱ ተዋግቶ በክብር መሞትን የሚመርጥ ፍጡር መሆኑ ነዉ። እኛ ሰዎች መፍራት የሚገባን ለነፃነት መሞትን ሳይሆን ያለነፃነት መኖርን ነዉ። ነፃነት ደግሞ የወያኔ ካድሬዎች እንደሚሰብኩን በኤኮኖሚ ካደግን በኋላ እነሱ የሚሰጡን ምፅዋት ሳይሆን ነፃነት የኤኮኖሚና የማህበራዊ ዕድገታችንን የሚያፋጥን የትግላችን ትልቁና ዋነኛዉ ግብ ነዉ።

በኮሎኔል መንግስቱ ዘመን ሁሉም ሰዉ ኢትዮጵያን እናቴ ወይም እናት አገር እያለ ይጠራት ነበር፤ ዛሬም ከወያኔ ሹሞች አንደበት ባይደመጥም ብዙ ሰዉ ኢትዮጵያን እናት አገር እያለ ሲጣራ ይደመጣል። ለመሆኑ ማነዉ የኢትዮጵያ ልጅ? ማነዉ እዉነተኛዉ የኢትዮጵያ ልጅ? - ማነዉ እንደ መቅደላዉ ጀግና "አንቺ እማማ ቃልኮ የእምነት ዕዳ ነዉ እንጂ የእናት የአባትኮ አይደለም" ብሎ እየፎከረ እናት አገሩን ከዘረኞችና አይን ካወጡ ዘራፊዎች ለማደን እንደ አፄ ቴዎድሮስ የክብር መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጀ? እናት አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ልጆች ወልዳለች- እዉነተኛዎቹ ልጆቿ ግን ይህንን ጥያቄ በአዎንታ ለመመለስ የተዘጋጁ ብቻ ናቸዉ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የመጨረሻዉ ደወል . . .

(ከገጽ 3 የዞረ)

እዉነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች የነሱና የእናት አገራቸዉ የኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል ለኢትዮጵያም ሆነ ለዜጎቿ ምንም ደንታ በሌላቸዉ ዘረኞች ሲወሰን ቁጭ ብለዉ አይመለከቱም። አገራችንን ላለፉት ሃያ አመታት የመሩት የወያኔ መሪዎች ወዴት እየወሰዱን እንደሆነ ሁላችንም የተረዳን ይመስላል፤ስለዚህ ለአገራችን አንድነትና ለልጆቻችን ነፃነት፤ እኩልነት፤ ሠላምና ብልጽግና የምንቆረቆር ኢትዮጵያዉያን አንድ ትልቅ ነገር ማድረግ የሚገባን ግዜ ቢኖር ያ" ግዜ አሁን ነዉ።

እኛ ኢትዮጵያዉያን ረጂም የነፃነትና የዲሞክራሲ ጉዞ ተጉዘን ዛሬ የመጨረሻዉ ምዕራፍ ላይ ደርሰናል። ይህንን የነፃነት ጉዞ በድል እንዳናገባድድ መንገዳችን ላይ ተገትሮ ደንቃራ የሆነብን ወያኔዎች የጫኑብን የፍርሀት መንፈስ ነዉ እንጂ የነሱ ጥንካሬ ወይም ግዙፍነት አይደለም። ፍርሀት ደግሞ ጥላዉ ነዉ እንጂ ትልቅ እሱ ራሱ እዚህ ግባ የማይባል ትንሽ ነገር ነዉ። መለስ ዜናዊ የለየለት ጨካኝ ሰዉ ስለሆነ ከቱኒዝያዉ ቤን አሊና ከግብፁ ሞባረክ የተለየ መላ ያስፈልገዋል ብሎ በከፍተኛ ጥንቃቄ ለህዝባዊ ለዉጥ መዘጋጀት ኢትዮጵያዊ አርቆ አስተዋይነት ነዉ። በፍርሀት እጅና እግርን አስሮ ለባርነት እጅ መስጠት ግን ከኢትዮጵያዊነት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ከሰዉ ልጆች ባህሪይ ዉጭ መሆን ነዉ። ነፃነታችንንና አገራችንን እየረገጠ ለሚገዛን ኃይል ለዚያዉም ህዝባዊ መሠረት ለሌላዉ አናሳ ኃያል አስረክበን የምንተኛዉ እያንዳንዱ መኻታ ሊቆረቁረን ይገባል። የወያኔ ዘረኞች ኢትዮጵያዊነትን ለማደብዘዝና የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጦ ለመግዛት የ17 አመት መስዋዕትነት ከከፈሉ እኛማ እነሱ ከጫኑብን ዉርደትና ዘረኝነት ለመላቀቅ ምን የማንከፍለዉ መስዋዕትነት ሊኖር ይችላል? ነፃነት የጎደለዉና ጀግንነት ያልጎበኘዉ ህይወት በቁሙ የሞተ ህይወት ነዉ፤ ጀግና ማለት ደግሞ ፍርሀት በፍፁም የሌለበት ሰዉ ማለት አይደለም- ጀግና ማለት ከፍርሀት ባሻገር ትልቅ ነገር እንዳለ በዉል የተረዳና ፍርሀቱን ዉጦ ይህንን ትልቅ ነገር ለመጨበጥ ህይወቱን ጭምር ለመሰዋት ፍቃደኛ የሆነ ሰዉ ነዉ! ስለዚህም ነዉ ያለ መስዋዕትነት ድል የለም የሚባለዉ!

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚታየዉን ዘረኝነት፤ፍትህ አልባነትና አይን ያወጣ ዝርፍያ ጋዜጣ ላይ አንብበን የምንረሳዉ ወይም በሬዲዮ ሰምተን ከንፈራችንን መጥጠን የምናልፈዉ ጉዳይ አይደለም። አርዶ ሊበላዉ ከሚዘጋጅ ጠላቱ ጋር ተመቻምቾ የሚኖር ለማዳ እንስሳ ብቻ ነዉ። እንስሳም ቢሆን አንዳንዴ ሲነሳበት ጠላቱን አሳድዶ ሲቦጫጭቅ በተደጋጋሚ ሰምተናል።ታዲያ የኛ ትከሻ ምን ያህል ተሸካሚ ቢሆን ነዉ እነዚህን ግዑዟ መሬት እንኳን የከዳቻቸዉን የቀን ጅቦች 20 አመት ሙሉ የተሸከምናቸዉ? እስከመቼ ነዉ ሂዱ ሲሉን ሄደን፤ ሲገፉን ተገፍተን፤ ሲረግጡን ተረግጠን አሜን ብለን የምንኖረዉ? በያንዳንዳችን ላይ መጡብን፤ በግዛት አንድነታችን ላይ መጡብን፤ በመብታችንና በነፃነታችን ላይ መጡብን- ከዚህ በላይ ምን እስኪያደርጉን ነዉ የምንጠብቀዉ? እነሱኮ ካሁን በኋላ የሚያደርጉት ምንም ነገር የለም! ካሁን በኋላ የቀረዉ ነገር እኛ ምን እናደርጋለን የሚለዉ ጥያቄ ብቻ ነዉ። ነፃነታችንን አሜሪካኖች አይሰጡንም- እንግሊዞችና ጀርመኖችም ነፃ አያወጡንም። እዉነቱን ለመናገር ተንበርክከን ስንፀልይ ብናድርም እኛ ያልታገልንለትን ነፃነት እግዚአብሐሬርም ቢሆን አይሰጠንም- እሱ አንዴ ሰጥቶናል። ከዛሬ በኋላ የኢትዮጵያ ነፃነት ብቸኛ ምንጭ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ እንደሆነ ሁላችንም ልንረዳ ይገባል። ስለዚህ በአንድ በኩል ልክ እንደ ግብፅ ህዝብ ክርስትናና እስልምና ሳይለያየን ወይም በዘር ሳንከፋፈል፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ሊቢያ ህዝብ የመሳሪያዉ ጋጋታና የቃላት ማስፈራሪያ ሳይበግረን ባጭር ግዜ ዉስጥ ዝግጅታችንን አጠናቅቀን የወያኔን ስርዐት በህዝባዊ ትግል ማስወገድና ነፃነታችንን ማስመለስ የእያንዳንዳችን ሐላፊነት ነዉ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ትግል ነፃ ትወጣለች!

---

## የእስልምና እምነት ተከታዮች በጂማ ክርስትያኖች

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዜና የአራት ኪሎ ነዋሪዎች ከወያኔው ሆድ አደር ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ጋር መጋጨታቸው የተገለጸ ሲሆን የአለም ገና ነዋሪዎች ደግሞ የከተማው ከንቲባ ጋዝ ተርከፍክፎበት ካልተቃጠለ አንረካም ማለታቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቲለኢቪዥን ኢሳት በዘጋብው ላይ አሳይቱአል።

ሰሞኑን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡን ያናገርናቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የፖለቲካ ፓርቲ አባል በስልክ በሰጡን አስተያየት በጋሞጎፋ፣ አዋሳና፣ ጂማ እየተከሰቱ ያሉ ግጪቶጭና ህዝባዊ አመጾች ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ለከት ያጣ ግፍ መለያ ናቸው ብለዋል። አያይዘውም ዘረኛና ከፋፋዩ አጋዛዝ እንዲህ አይነት ግጪቶችን ራሱ እንደሚያስነሳና ኢትዮጵያዊያን በነኝህ አነስተኛ ችግሮች ትኩረት በማድረግ ስርአቱ እያደረሰ ያለውን መረን የለቀቀ በደል እንዲረሳ፣ እርስ በርሱ በማጋጨት እንዲከፋፈል እንደሚያደርግ ገልጸው፣ በውጪ ሃገራትም ሆነ በሃገር ውስጥ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን አሁን የተገኘውን አጋጣሚ በአግባቡ ልንጠቀምና ዘረኛውን አገዛዝ ከትከሻችን አሽቀንጥረን ለመጣል በአንድነት የመቆሚያ ጊዚያችን ነው ብለዋል።

## የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ ባለቤት የሆነቺው አዜብ መስፍን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተመሳሳይ መልኩ ቀደም ብሎ በወጣ ዘገባ ኤቢሲ የተባለው የስፔን ጋዜጣ አዜብ መስፍን አባካኝ የሆነች ሴትና በአውሮፓና በአሜሪካ በሚገኙ ውድ ሱቆች ውስጥ እቃዎችን እንደምትገዛ የሚገልጽ መረጃ ከአወጣ በሁዋላ፣ አዜብ የአውሮፓ ጉዞዋን ገትታ በዱባይ እቃዎችን ለመግዛት ተገድዳ ሊሆን እንደሚችል ተገምቱአል። ጋዜጣው አዜብ መስፍን የባሉዋ ሀብት ከሆነው ከ1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዩሮ ወይም ወደ 33 ቢሊዮን ብር ከሚጠጋ ሀብት ውስጥ እያፈሰች እጅግ ውድ የሚባሉት እቃ እንደምትገዛ አጋልጧል።

በሚሊየን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በቀን አንድ ጊዜ መብላት ተስኑአቸውና የለት ከለት ኑሮአቸውን መግፋት አቅቶአቸው በሚገኙበት በዚህ ወቅት የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ ባለቤት አዜብ መስፍን እጅግ ውድ የሆኑ እቃዎችን በግል አውሮፕላን እየተዟዟረች የምታደርገው ሽመታ በርካታ ኢትዮጵያውያንን የሚያስቆጣ ተግባር ነው።

ይህ በንዲህ እንዳለ የቱኒዚያው ቤን አሊ መኖሪያ ቤቴመንግሥት ሲፈተሽ በመቶ ሚሊየኖች የሚቆጠር ዶላር እንዲሁም ውድ ጌጣጌጦች ደብቆ መገኘቱን የተመለከቱ አንድ በውጭ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊ በሰጡት አስተያየት፣ የቤን አሊ አይነት ዝርፊያና ብልግና በእጥፍ ሃገራችን ውስጥ በነ አዜብ መስፍን ብቻ ሳይሆን በዙሪያቸው በተኮለኮሉ ዘረኞች ጭምር እየተፈጸመ መሆኑን ገልጸው፣ ኢትዮጵያም ውስጥ እንደነ ቤን አሊ ዘረፋው የሚቆምበትና ሌቦቹም የሚጋለጡበት ጊዜ ሩቅ አይደለም ብለዋል።

## ወያኔ አርሶ አደሮችን የፓርቲ አባል ካልሆናችሁ እያለ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የወያኔ ባለስልጣናቱም ለአርሶ አደሮች በተዘረጋው የህዋስ አደረጃጀት አልተሳተፉም የተባሉትን አርሶ አደሮች ዝርዝር ሪፖርት እንዲያደርጉ ያስጠነቀቁዋቸው ሲሆን አንሳተፍም ያሉት የተቃዋሚ ድርጅት አባላት መሆን አለባቸው ዋጋቸውን ይከፍላሉ ሲሉም መደመጣቸው ተገልጾአል።

ዘጋቢያችን ያናገራቸው ስብሰባው ላይ ተሳታፊ የነበሩ አንድ አርሶአደር ስለጉዳዩ ተጠይቀው ሲመልሱ፡ ዱሄ ምን ዱበጀናል ብለው እንደሚያደርጉት ግራ የገባቸው መሆኑን ተናግረው ልብ ከሸፈተ ምን ቢያደርጉለትስ መች በቀላሉ ይመለሳል፡ እስከዛሬ በመልካም ስራ በልማት ያልጎበኙንን ዛሬ የኛ አባል ሁኑና ጥቅም እንሰጣቸሁዋለን በማለት ማስገደዱ "ቀድሞ ነበር እንጂ መጠኖ መደቆስ ሁዋላ ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ" የሚለውን ስንኝ አስታወሰኝ ባማለት ምሬታቸውን ተናግረዋል። አዛውንቱም አያይዘው አብዛኞቻችን አዛውንቶች ነን እንግዲህ እማ እኛን ምን ያደርጉናል ባይሆን ልጆቻችን የነዚህ መሰሪዎች ቀንበር እንዳያርፍባቸው መታገል ነው እንጂ ሁለት ጊዜ ሞት የለ ባማለት ቁጭታቸውን ገልጸዋል።

## ወያኔ በያዝነው የበጀት አመት ወደ ውጪ የላከው የቡና ምርት

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አገሮች በመላክ ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኘውን የጫት ንግድ በሸርክና ስም ገብታ የተቆጣጠረቿው የዘረኛው መለስ ዜናዊ ባለቤት አዘብ መስፍን የቡናውንም ንግድ ለመጠቅለል በስውር እየተንቀሳቀሰች እንደሚትገኝ ከአድስ አበባ ነጋዴዎች ምክር ቤት አካባቢ የተገኘ መረጃ አጋልጦአል። አዜብ መስፍንና አብረዋት የዘረፋ ተባባሪ የሆኑ የንግድ ሽሪኮቿ ወደውጪ የሚልኩዋቸውን ምርቶች ከአምራቹ በርካሽ ዋጋ ለመሸመት እንዲያመቻቸው በተለያየ ጊዜ የአለም ገበያ ላይ ይህ ምርት ዋጋው ወድቆአል የሚል የሃሰት መረጃ በማሰራጨት ከድሀው ገበሬ ምርቱን እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ እንደሚሰበስቡ ይታወቃል። ባለፈው አመት መጨረሻ ገደማ ወደ ውጪ ይላካል ተብሎ ተዘጋጅቶ የነበረ ከ10000 አስር ሺ ቶን በላይ ቡና ከነበረበት መጋዚን ወጥቶ የት እንደደረሰ ሳይታወቅ እንደቀረና በቅርቡ ተመሳሳይ መጠን ያለው ቡና በአዜብ መስፍን ት ዕዛዝ በድብቅ ከአገር ወጥቶ እንደተሸጠ እንደተደረሰበት ይህ መረጃ ያገኙ የፓርላማ አባላት በስብሰባ ላይ ጥያቄ አቅርበው መለስ ዜናዊ ያለፈው አልፉዋል ከንግዲህ እንዲህ አይነት ህገወጥ ተግባር አይደገምም በማለት ተናግሮ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

ከድህው ህዝብ ጉሮሮ ላይ እየነጠቁ በውጭ ሀገራት ባንኮች የሚያከማቹትን ሀብት የት ሊበሉት አስበው ነው በማለት አስተያየቱን የሰጠ አንድ ዘጋቢያችን ያናገረው የአዲስ አበባ ወጣት እነመለስ ሰሞኑን እንኩዋን አምባገነን ጉዋደኞቻቸው ላይ እየደረሰ ከለው ውድቀት መማር አለመቻላቸው አስገርሞኛል። እርግጠኛ ሆኜ የምናገረው ግን በዚህ ሁኔታ እንደማይቆዩ በሚገባ የተረዱ መሆኑን ሲሆን ለዚህም ሰሞኑን በየከተማው የሚያደርጉት ግርግር በቂ መረጃ ነው። ጥያቄው መቼ የሚለው ነው እንጂ ፡ ግፉ ዝርፊያውና መከራውማ ከሚገባው በላይ አንገሽግሾናል በማለት አስተያየቱን ገልጾአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org